# የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የህግ ማዕቀፍ

## 1. መግቢያ

የካፒታል ገበያ በአዋጅ ቁጥር 1248 / 2016 መውጣቱ በሀገሪቱ የፋይናንስ ስርአት ላይ ከፍተኛ ለውጥ እንደሚያመጣ ይታመናል። በዚህ የካፒታል ገበያ ሥነ-ምህዳር ውስጥ ካሉት ቁልፍ ተዋናዮች መካከል የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ ዋናው ሲሆን ሚናውም የገበያ ተደራሽነትን በማመቻቸት እና የኢንቨስተሮችን እምነት በመጠበቅ ግብይትን ማሳለጥ ነው።ይህ ጽሁፍ በአዋጁ እና በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ መሠረት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ ምንነት፣ የፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶች፣ የሥራ ክንዋኔዎች እና የቁጥጥር ሥራዎችን ይተነትናል።

## 2. የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ ምንነት

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ ማለት ኮሚሽን እየተከፈለው በደንበኞቹ ስም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የመሸጥ እና የመግዛት ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው። በካፒታል ገበያ አዋጅ አንቀጽ 2(33) መሠረት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ በግልጽ ትርጉም ተሰጥቶት ይገኛል።ይህ ደላላ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ በማግኘት እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አባል በመሆን በደንበኞች ስም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የመግዛት እና የመሸጥ ሥራ ያከናውናል።ይህም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ደላላ እንደ መሐከለኛ የግብይት አሳላጭ የሚያስቀምጥ ሆኖ በራሳቸው መለያ ለራሳቸው ከሚነግዱ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ አከናዋኝ (Securities Dealer) የተለዩ አድርጎ ያስቀምጣቸዋል። የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ በኢንቨስተሮች እና በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ መካከል እንደ ድልድይ ሆነው ያገለግላሉ። በደንበኞቻቸው በሚሰጣቸው ትእዛዝ ወይም መመሪያ ላይ ተመስርተው የግብይት ማለትም የሰነደ ሙአለ ንዋይ ሽያጭ እና ግዥ ያከናውናሉ።

***"የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ ማለት ኮሚሽን እየተከፈለው በደንበኞቹ ስም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የመሸጥ እና የመግዛት ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው።"***

## 3. ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ የተፈቀዱ ተግባራት

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ በሰነደ ሙአለ ንዋዮች ግብይት ሚናው የጎላ ሲሆን የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፦

- ፈቃድ ባላቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎች ላይ ለደንበኞች የግዢ/ሽያጭ ትዕዛዞችን ይፈጽማሉ፣
- የገበያ መረጃ ለኢንቨስተሮች ያስተላልፋል
- በሁለተኛ ደረጃ ገበያ ግብይቶች ውስጥ እንደ ወኪል ሆነው ያገለግላሉ፣
- የደንበኛ ትዕዛዞችን በፍጥነት ፣ ትክክለኛነት እና ፍትሃዊነት ይቀበላል፣ ያስኬዳል እናያስፈጽማል፣
- በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የተመዘገቡ እና ግብይት የሚደረግባቸው ሰነዶችን ለኢንቨስተሮች ያሳውቃል፣
- የግብይት ማረጋገጫዎችን ያወጣል እንዲሁም ለደንበኞች የተፈጸሙ ግብይቶችን መዝገቦችን ይይዛል።
- በወንጀል የተገኘ ሃብትን እውነተኛ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መደገፍ እንዲሁም ደንበኛህን እወቅ መርሆች ጋር በተያያዘ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን መመሪያዎችና ትእዛዞች መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ ለተግባራዊነት የራሱን አሰራር ይዘረጋል፣
- ለደንበኞች የገበያ አሰራሮች፣ ስጋቶች እና የግብይት ሂደቶችን በተመለከተ መሰረታዊ መመሪያ ይሰጣል፣

- በድህረ-ግብይት የሚከናወኑ የክፍያ እና ርክክብ ሥራዎችን ፈቃድ በተሰጠቸው የክፍያ ርክክብ እና ማከማቻ ተቋማት እንዲፈጸም ያመቻቻል። እንደዚሁም ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን ያከናውናል።

በመሆኑም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ በሰነደ ሙአለ ንዋይ ገበያ ቅልጥፍናን፣የዋጋ ግኝትን እና የኢንቨስተሮችን ጥበቃ በማረጋገጥ ረገድ ሚናው ወሳኝ ነው።

## 4. የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ ፍቃድ መስፈርቶች አጠቃላይ መስፈርቶች

የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ የሚሹ አመልካቾች እንደ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁ. 890/2016 መሰረት ማመልከቻ ከዝርዝር ሰነዶች እና መግለጫዎች ጋር መቅረብ አለባቸው። መስፈርቶቹ በአመልካቹ የፈቃድ ጥያቄ አይነት ላይ ተመስርተው የሚለያዩ ቢሆንም የጋራ የቁጥጥር እና ፋይናንስ መረጃን ይፋ የማድረግ የአሰራር ስርዓት ከሌሎች የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ይጋራሉ።

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ ፈቃድ አመልካች በአክሲዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማኅበር አይነት የተደራጀ ሆኖ የሚከተሉትን ጠቅላላ መስፈርቶች እና ሰነዶች በማሟላት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።ከፍ ብሎ በተጠቀሰው መመሪያ በተደነገገው መሠረት

- በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ ትክክለኛ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ፣ እና የመመስረቻ ጽሁፍ፣
- ድርጅቱ በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ዘርፍ እንዲሰራ ዳይሬክተሮች ወይም ሸሪኮች የወሰኑበትን ቃለ-ጉባኤ እና
- የአመልካቹ ባለአክሲዮኖች እና ከፍተኛ ባለአክሲዮኖች ተለይቶ ዝርዝር መቅረብ አለባቸው።

ከዚህ በተጨማሪ አመልካቹ የረዥም ጊዜ ስትራቴጂውን፣ የሚቀርቡ አገልግሎቶችን፣ ከሚዘረዝር አጠቃላይ የንግድ እቅድ፣ የአመልካች እና በሱ እንዲሾም የታቀደው የእጩ ተሿሚ እንደራሴው (Proposed Appointed Representative) የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች የሥነ-ምግባር ደንቡን እና ሁሉንም የሚመለከታቸው የካፒታል ገበያ ህጎችን በማክበር ለመስራት መስማማታቸውን የሚያሳይ ስምምነት ማቅረብ ይጠበቅበታል። እንደዚሁም አመልካቹ ለ12 ወራት ወይም ከዚያ በላይ የሠራ ከሆነ፣ የበጀት አመቱን የሂሳብ መግለጫ አካውንት ማቅረብ ይጠበቅበታል።

በተጨማሪ አመልካቹ ከዝቅተኛው የካፒታል መስፈርቶች ጋር በተመሰከረለት ሂሳብ አዋቂ የተሰራ የተጣራ ሀብት ማስረጃ ማቅረብ ያለበት ሲሆን በዚህ ረገድ ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ ፈቃድ ለማግኘት የተቀመጠው የተጣራ ሀብት መስፈርት ብር 6,000,000 (ስድስት ሚሊዮን) ነው።

ሌሎች የቴክኖሎጂ ደህንነት፣ የውስጥ ቁጥጥር እና የስጋት አስተዳደር ደረጃዎችን እና አሰራሮችን ማክበር፣ ደንበኞቹን ጠንቅቆ ማወቅ የሚያስችለውን (Know Your Client) አሰራር ሥርዓት መዘርጋት ጨምሮ የደንበኛ መለያ መክፈቻ ቅጾች ናሙና ማቅረብን እንዲሁም በባለሠልጣኑ የሚወሰኑ ሌሎች የቁጥጥር መስፈርቶችን የሚያሟላ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅበታል። ደንበኛን ጠንቅቆ ከማወቅ ጋር ተያያዞ የሰነደ ሙአለ ንዋይ ደላሎች ግዥ ወይም ሽያጭ የሚፈጽሙላቸውን ኢንቨስተሮች የገንዘብ ምንጭ መጠየቅ እና ተገቢውን ፎርማሊቲ ማክበራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። ይህም በወንጀል የተገኘ ሀብት እውነተኛ በማስመሰል ወደ ካፒታል ገበያ እንዳይገባ እና የካፒታል ገበያ በህገ ወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብ ማጠቢያ እንዳይሆን እንዲሁም ከዚህ የሚገኘው ገንዘብ

ሽበርተኝነትን ለመደገፍ እንዳይውል ደላላው ማጣራት ያለበትን ሁሉ በትጋት ለማጣራት የሚያስችል የአሰራር ስርአት መዘርጋቱን ማሳየት ይጠበቅበታል።

አመልካቹ ለትምህርት እና ለሙያ ብቃቶች የስርዓት ትምህርት ዝግጅት እና ደጋፊ ሰነዶች ማዘጋጀት፣ በመመሪያው በተቀመጠው የሰርተፊኬሽን ስታንዳርድ መሰረት በቂ የትምህርት ዝግጅት፣ የስራ ልምድ እና ተዛማጅነት ያለው የካፒታል ገበያ ስልጠና የምስክር ወረቀት ያለው ሰራተኛ መቅጠሩን ማስረጃ ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት። ፈቃድ ጠያቂው የውጪ ኩባንያ ከሆነ ከተመዘገበበት ሀገር ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ጥሩ አቋም ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

እነዚህ መስፈርቶች ሲሟሉ ፈቃድ ለሚጠየቅበት ዘርፍ የተቀመጠ ክፍያ ክፍሎ ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅበታል።

## 5. የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ የብቃት መስፈርት

በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ መሰረት፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ ፈቃድ የሚፈልጉ አመልካቾች ከላይ ከተዘረዘሩ ጠቅላላ መስፈርቶች በተጨማሪ ብቁ እና ተገቢ የሆኑ ባለሙያዎችን ጨምሮ ዋና የሕግ ማስከበር መኮንን እና ሌሎች ተወካዮችን መሾም አለበት።

በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፍቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ መሰረት እንደ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ ሆነው ለመስማራት የሚፈልጉ አመልካቾች በአንቀፅ 7(1) የተዘረዘሩትን አጠቃላይ የፈቃድ መስፈርቶች ብቻ ሳይሆን የቅድመ ማረጋገጫ ምርመራ ከማድረጋቸው በፊት ተጨማሪ ሁኔታዎችን ማሟላት አለባቸው። በተለይም የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን ከታወቀ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም ካልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ በመርህ ደረጃ የጸደቀ የግብይት ፈጻሚ አባልነት ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሊጠየቁ ይችላሉ። ይህ ቅድመ ሁኔታ አመልካቹ ፈቃድ ሲሰጥ በገበያ ስራዎች ላይ በንቃት ለመሳተፍ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል።

## 6. የስነ-ምግባር ደንብ

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ የሚከተሉትን የካፒታል ገበያ አገልግሎት አቅራቢዎችን የስነ-ምግባር ደንብ ማክበር አለበት።

የደንበኞች ትክክለኛ መረጃ መያዝ፣ የደንበኛ ግብይቶችን ዝርዝር መዝገቦችን መያዝ፣

- የጥቅም ግጭቶችን ማስወገድ፣
- የደንበኛ መረጃ ምስጢራዊነት መጠበቅ፣
- የንግዶችን ወቅታዊ አፈፃፀም ሪፖርት ማድረግ፣ ስለ የግብይት መጠኖች፣ የደንበኛ ያላቸውን የደንበኛ መጠን እና ህጎችን የማክበር ሁኔታ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ፣ ማናቸውንም የአሰራር እና የህግ ጥሰቶች ወይም የአሠራር ስጋቶች ይፋ ያድርጉ፣

እነዚህን እና ሌሎች በሥነ-ምግባር ደንቡ ላይ የተገለጹትን የአሰራር ሥርዓቶች አለማክበር መታገድ ወይም ፍቃድ መሰረዝን ጨምሮ ሌሎች አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ሊያስከትል ይችላል።

ሌላው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ በመመሪያው መሰረት የሚከተሉትን እንዲያቋቁሙ ይጠይቃል።

- ከደንበኞቹ ጋር በሚኖረው ግንኙነት የውስጥ ቁሬታ አያያዝ ዘዴዎች መዘርጋት፣
- አለመግባባቶችን ለመፍታት ግልፅ ሂደቶች፣
- በምርመራዎች እና ህግ ማስከበር እርምጃዎች ከባለሥልጣኑ ጋር መተባበር አለበት።

እነዚህ ሁኔታዎች የኢንቨስተሮችን እምነት ለማሳደግ እና የገበያ ታማኝነትን ለማስጠበቅ ያለሙ ናቸው።

## 7. ፈቃድ የመመለስ አሰራር

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ ፈቃዱን ለመመለስ ሲያስብ በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ አንቀጽ 36 የተመለከቱትን

የደንበኞችን ጥቅም ለመጠበቅ እና የገበያ ቀጣይነትን ለማረጋገጥ የተነደፉትን ተጨማሪ ግዴታዎች ማክበር ይኖርበታል።

እንደ የመውጫው ሂደት፣ ደላላው ከተተካው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ ጋር መደበኛ ስምምነት ማድረግ ይጠበቅበታል። ይህ ስምምነት ተተኪው ደላላ የሚወስዳቸውን ሙብትና ግዴታዎች እና እዳዎች ማስተላለፍን ጨምሮ የተተኪ ውሎችን በግልፅ መግለጽ አለበት። የዚህ ውል ዋነኛው አላማ ተተኪው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላላ ለደንበኞች ያልተቋረጠ አገልግሎትን የሚሰጥ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ እንደ ህጋዊ እና ተግባራዊ ድልድይ ሆኖ ማገልገል ማስቻል ነው።

ፈቃዱን የሚመልሰው ደላላ የደንበኛ ሂሳቦችን እና ሀብቶችን ሁሉንም መዛግብት ለኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን ማቅረብ አለበት። እነዚህ መዝገቦች የደንበኛ ሂሳቦችን ወደ ተተኪው ደላላ ለማስተላለፍ የተቋቋሙትን ዘዴዎች በዝርዝር ማሳየት አለባቸው፣ ይህም የተተኪውን ደላላ ማንነት እና የብቃት ሰነዶችን ሙሉ በሙሉ ይፋ ማድረግን ይጨምራል።

ደላላው የመውጫ ማስታወቂያ ለደንበኞቹ የአንድ ወር የማስታወቂያ ጊዜ ካለቀ በኋላ በአስራ አራት (14) ቀናት ውስጥ ሂሳባቸውን እና ተያያዥ ንብረቶቻቸውን ወደ መረጡት ኢላማ ተደራጊ ደላላ ማስተላለፍ እንደሚጠበቅባቸው ማሳወቅ አለበት። በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ አንድ ደንበኛ ተመራጭ ደላላ ለመሾም ካልቻለ፣ የሚወጣው ደላላ የደንበኞቹን ሂሳቦች እና ሀብቶችን ወክሎ የሚያስተዳድር ተተኪ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ የመሾም ግዴታ አለበት።

ይህንን ሽግግር ለማመቻቸት ደላላው ሁሉንም ደንበኞቻቸውን፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችና ፖርትፎሊዮቻቸውን፣ መዝገቦቻቸውን ማጋራት፣ ሌሎች ተዛማጅ ሀብቶችን እና በእያንዳንዱ መለያ የተመደበውን የሚመለከተውን ኢላማ ወይም ተከታይ ደላላ የሚያሳይ ዝርዝር መርሃ ግብር ማዘጋጀት አለበት። ይህ የጊዜ ሰሌዳ በእያንዳንዱ የደንበኛ መለያ ውስጥ የተያዘውን የገንዘብ ሒሳብ ማካተት አለበት።

ፈቃዱን ከመመለሱ በፊት ደላላው ሁሉንም በመጠባበቅ ላይ ያሉ የደንበኛ ትዕዛዞችን መፈጸም ይጠበቅበታል። ይህን ማድረግ ካልቻለ፣ ተተኪው ደላላ ከሽግግሩ በኋላ የተሰጣቸውን ግዴታዎች እንዴት እንደሚወጣ የሚገልጽ የጽሁፍ አሰራር ማቅረብ ይጠበቅበታል።

ከዚያም ደላላው የተዘጋጀውን የድርጊት መርሃ ግብር ከሁሉም ደጋፊ ሰነዶች ጋር በማደራጀት ወደተዘጋጀለት ኢላማ ወደተደረገው ወይም ለተተኪው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ ማስተላለፍ አለበት። ይህ ዝውውር እንከን የለሽ መሆን ያለበት ሲሆን ይህም ከደንበኛ ጋር የተገናኙ ሁሉም መዛግብት እና ሀብቶች ደህንነቱ በተጠበቀ እና በትክክል መተላለፋቸው መረጋገጥ አለበት።

በተጨማሪም ደላላው ከገበያ ለመውጣት ያለውን ፍላጎት ለማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ማሳወቅ ይጠበቅበታል። ይህ ማስታወቂያ ፍቃድ ለመመለስ ለባለሥልጣኑ ከቀረበው መደበኛ ማመልከቻ ጋርተያይዞ መቅረብ ይጠበቅበታል።

በመጨረሻም፣ የተተካው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ በሁሉም የተላለፉ የደንበኛ መለያዎች ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። ይህም የእያንዳንዱን መለያ ሁኔታ ከደንበኛው በቀጥታ ማረጋገጥን የሚያካትት ሲሆን ይህም የሽግግሩን ትክክለኛነት እና የቁጥጥር ደረጃዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል።

Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal